የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፶
አዲስ አበባ ነሐሴ ፲፭ ቀን ፲፱፻፺፱

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

13th Year No 50
ADDIS ABABA 21st August 2007

<u>ማውጫ</u>

አዋጅ ቁጥር ፭፻፵/፲፱፻፺፱ ዓ.ም

በሰነዓ ፎረም አባል አገራት መካከል በጉምሩክ ዙሪያ በጋራ ለመሥራትና ኮንትሮባንዳንና ሕገ-ወጥ ንግድን ለመከላከል የተደረገው የትብብር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ … ገጽ ፫ሺ፯፻፴፪

<u>CONTENTS</u>

**Proclamation No. 540/2007**

Agreement on Customs Cooperation and Anti-smuggling and Illicit Trafficking between the member States of the Sana'a Forum Ratification Proclamation Page 3732

## አዋጅ ቁጥር ፭፻፵/፲፱፻፺፱

## በሰነዓ ፎረም አባል አገራት መካከል በጉምሩክ ዙሪያ በጋራ ለመሥራትና ኮንትሮባንድንና ሕገ-ወጥ ንግድን ለመከላከል የተደረገውን የትብብር ስምምነት <u>ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ</u>

በሰነዓ ፎረም አባል አገራት መካከል በጉምሩክ ዙሪያ በጋራ ለመሥራትና ኮንትሮባንድንና ሕገ-ወጥ ንግድን ለመከላከል የሚያስችል የትብብር ስምምነት ሐምሌ ፲፩ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም በአዲስ አበባ ኢትዮጵያ የተፈረመ ስለሆነ፣

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፳፪ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፣

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ /፩/ እና /፲፪/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "በሰነዓ ፎረም አባል አገራት መካከል በጉምሩክ ዙሪያ በጋራ ለመሥራትና ኮንትሮባንድንና ሕገ-ወጥ ንግድን ለመከላከል የተደረገው የትብብር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፭፻፵/፲፱፻፺፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## PROCLAMATION NO. 540/2007.

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE AGREEMENT ON CUSTOMS COOPERATION AND ANTI-SMUGGLING AND ILLICIT TRAFFICKING BETWEEN THE MEMBER STATES OF THE SANA'A FORUM

**WHEREAS,** the Agreement on Customs Cooperation and Anti-smuggling and Illicit Trafficking between the member States of the Sana'a Forum was signed in Addis Ababa, Ethiopia on the 18th day of July, 2006;

**WHEREAS,** The House of Peoples' Representative of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its session held on the 29th day of June, 2007;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 Sub-Article (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Agreement on Customs Cooperation and Anti-smuggling and Illicit Trafficking between the member States of the Sana'a Forum Ratification Proclamation No. 540/2007."

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

**፪. ስምምነቱ ስለመጽደቁ**

በሰንዓ ፎረም አባል አገራት መካከል በጉምሩክ ዙሪያ በጋራ ለመሥራትና ኮንትሮባንድንና ሕገ-ወጥ ንግድን ለመከላከል እንዲያስችል ሐምሌ ፲፩ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም. በአዲስ አበባ ኢትዮጵያ የተፈረመው የትብብር ስምምነት ጸድቋል።

**፫. የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለሥልጣን ሥልጣን**

ስምምነቱ በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ሥልጣን ለኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቷል።

**፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ነሐሴ ፰ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**2. Ratification of the Agreement**

The Agreement on Customs Cooperation and Anti-smuggling and Illicit Trafficking between the member States of the Sana'a Forum signed in Addis Ababa, Ethiopia on the 18th day of July 2006 is hereby ratified.

**3. Power of the Ethiopian Customs Authority**

The Ethiopian Customs Authority is hereby empowered to implement the Agreement

**4. Effective Date**

This Proclamation shall enter into force up on Publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 14th day of August, 2007**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**